# መልክ ስጠኝ እንጅ ሙያንስ…

ቻላቸው Chebudie@yahoo.com

ፈረንጆች እንደሚሉት # Politicians think about the next election, the states man think about the next generation; ወደ አማርኛ ስመልሰው #ፖለቲከኞች ስለመጪው ምርጫ ያስባሉ፤ብልህ የፖለቲካ መሪዎች ደግሞ ስለ መጪው ትውልድ; ይህ አባባል ለመራጩም ሆነ ለተመራጩ ጥሩ መልዕክት አለው፡፡

መጪው ምርጫ የመጪውን ትውልድ ሁለንተና የሚወስንበት ሁናቴ አለ፤ የሚቀጥሉት ዘመናት አገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች የሚገኙት በዛሬው ዘመን በሚመረጡ ፖለቲከኞች ወይም ብልህና ሕዝባዊ የፖለቲካ መሪዎች የብስለት ወይም የድክመት መዳፍ ውስጥ ነው፤ ይህም ፖለቲካዊ ስብዕና የሚታነፀው በተጨባጭ በአገሪቱ ሰፍኖ ባለው የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ እንደመሆኑ መጠን፤የፖለቲካ ሥርዓቱ ዴሞክራሲያዊ መሆን ወይም ያለመሆን የአሁኑንም ሆነ የሚቀጥለውን ትውልድ ሁለንተና ይወስናል፡፡ ነፃና ሕዝባዊ ምርጫ ዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት አንዱና ዋነኛ ገጽታ ነው፡፡

በአገራችን በየሥርዓተ መንግሥቱ የተለያዩ የምርጫ ሂደቶች ተካሂደዋል፡፡ በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመን በ1923 ዓ.ም. የወጣውም ሆነ በ1948 ዓ.ም. የተሻሻለው ሕገ-መንግሥት የንጉሡ ነገሥቱን ጥቅም የሚያረጋግጡ እንጂ ለሕዝቡ የፈየዱለት አንዳችም ጥቅም አልነበረም፡፡ በወቅቱ በነበሩት የሕግ መወሰኛና የሕግ መምሪያ ምክር ቤቶች አባላትም በፈጣሪ የተሰየመውን ንጉስ ለማማከርና ለመርዳት እንጂ የንጉሡን ፍቃድ ከመፈፀም የዘለለ ሥልጣን አልነበራቸውም፡፡ የደርግ ሥርዓት የወጣው ሕገ-መንግሥትም ቢሆን በሶሻሊዝም ርዕዮት ዓለም ላይ የተመሠረተ የወታደራዊውን መንግሥት ጥቅም ለማስጠበቅ እንጂ የሰፊውን ሕዝብ ጥቅም ያስቀደመ እንዳልነበር የቅርብ ጊዜ ትውስታ ነው፡፡ይሄ መወሳት ያለፉት ቅርብ ዘመናት የኢትዮጵያ ፖለቲካ ነባራዊ እውነታ ቁራጭ ሥዕል ነው፡፡

የደርግ መንግሥት ወድቆ አገራችን ወደ ሕገ-መንግሥታዊ የዴሞክራሲ ሥርዓት ሽግግር ማድረግ ከጀመረች ከ1983 ዓ.ም. በኋላ ሕገ-መንግሥቱን መሠረት ያደረጉ ሦስት አገራዊ

ምርጫዎች ተካሒደዋል፡፡ በ1987፣ በ1992 እና በ1997 ዓ.ም. የተካሔዱት ምርጫዎች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ አሁን ደግሞ በ2002 የሚካሄደው አራተኛው አገራዊ ምርጫ ከፊት ለፊታችን ይጠብቀናል፡፡

በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 54 መሰረት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ፣ ሁሉን አቀፍ፣ ነፃ ቀጥተኛ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በምስጢር በሚሰጥበት ሥርዓት ምርጫ በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ፡፡ በተመሳሳይ ሂደት ለክልል ምክር ቤት አባላትም ይመረጣሉ፡፡ የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምፅ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት እንደሚካሄድ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ይህ ሲሆን ነው ዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ሊካሔድ የሚችለው፡፡

ምርጫ ውድድር ነው፤ መሸነፈና ማሸነፍ ደግሞ የውድድር ውጤት ፀጋዎች ናቸው፡፡ በምርጫ የሚወደዳሩ አካላትም ሁሉ የአሸናፊነት ወኔ ሰንቀውና ጥሩ ስነ-ልቦና ይዘው ወደ ውድድሩ መግባት ጉብዝና ነው፡፡ ለማሸነፍ ወደ ውድድር መግባት ትክክለኛና ጤናማ እሳቤ ቢሆንም በዚያው ልክ ውድድር ነውና መሸነፍንም እኩል ታሳቢ ማድረግ ከሥልጡን የፖለቲካ ሰው ይጠበቃል፡፡ በምርጫ ተወዳድሮ ያላሸነፈ ፓርቲ ወይም ተወዳዳሪ ውጤቱን በፀጋ ተቀብሎ ለቀጣይ ምርጫ ጠንክሮ መሥራት እንዳለበትና አሸናፊውን በቅን ልቦና ‹‹እንኳን ደስ አለህ›› ብሎ በሰላማዊ መንገድ ውድድሩን ማጠናቀቅና ተከባብሮ የመስራትን ባህል የመገንባት፣ የመቻቻል፣ የመደማመጥና የመግባባት ልምድን ማዳበር ከስልጡን ፖለቲከኛ ይጠበቃል፡፡

ሁሉም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ግባቸው ህዝብንና አገርን ማገልገል እስከሆነ ድረስ ምርጫው ሰላማዊ፣ ፍትሐዊ፣ ነፃና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን በመመካከር ለችግሮች መፍትሔ በመፈለግ ለህገርና ለህዝብ ተቆርቋሪ ሆነው መስራት ይገባቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከምርጫ ማግሥት ጀምሮ የሕዝብን ይሁንታ ያገኘው ፓርቲ ሕዝብ የጣለበትን አደራ ጠንክሮ እንዲሰራ ጠንካራ ጎኑን በማወደስ ደካማ ጎኑን እንዲያጠናክር ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

እዚህ ላይ ያደጉ ሀገሮችን ተሞክሮ ማንሳት ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡ በተለይ በአሜሪካ ያስተዋልነውን ሁኔታ ማስታወስ በጣም ጠቃሚ ጉዳይ ነው፡፡ የቅርብ ጊዜውን ብንመለከት

እንኳን ፕሬዚደንት ኦባማ ከሪፐብሊካኑ ተፎካካሪያቸው ጆን ማኬን ጋር ያደርጉት የነበረው የምርጫ ውድድር በኦባማ አሸናፊነት ሲጠናቀቅ የመጀመሪያ የእንኳን ደስ ያለህ መልእክት ለኦባማ ያስተላለፉት ተቀናቃኛቸው ማኬን ነበሩ፡፡ ‹‹ መሪያችን በመሆንህ የተሰማኝን ደስታ የምገልፅልህ በታላቅ አክብሮት ነው፤ ለአገራችን ብልጽግናና ደህንነት አብረን እንሠራለን ›› የሚል መልእክት ነበር ያስተላለፉላቸው፡፡ ትክክለኛ ተቃዋሚ ማለት በዚህ መልኩ ልዩነትን ለህዝብ አሳውቆ ድጋፍ ማግኘት ሲችል ብቻ መሆኑን ያስመሰከረ ዴሞክራሲያዊ ምርጫ ማለት ይኼ ነው፡፡

የምርጫን ውጤት በፀጋ ተቀብሎ ለሀገር ልማትና ለህዝቦች ብልጽግና አብሮ ለመስራት መነሳት አገራዊ ራእይ ካላቸው በሳል ፖለቲከኞች የሚጠበቅ ቢሆንም በተቃራኒው የተሰለፉ አንዳንድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የአሄውን የምርጫ ሥርዓት የሚናፍቁ ዛሬም ድረስ አለመጥፋታቸው በጣም ያስገርማል፡፡ በምርጫ ካላሸነፍኩ ሥልጣንን በጎዳና ላይ ነውጥ አገኛለሁ ብሎ የአመጽ መንገድን መምረጥ፣ ሀገራችን የጀመረችውን የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ የሚያደናቅፍ ሂደት ነው፡፡ በምርጫ ካላሸነፍኩኝ ምርጫው ተጭበርብሯል፣ ኮሮጆው ተሠርቋል በማለት በሕገ-መንግሥቱ የተሰጠውን መብት ተጠቅሞ ሕገ-ወጥ ንግግርን በአደባባይ መለፈፍ ለሀገራችን የሚበጅ አይደለም፡፡ ቀድሞውንም ራዕያቸው አገርንና ህዝብን ማገልገል ሳይሆን ዋናው ግባቸው ሥልጣን ላይ ለመውጣት ስለሆነ መርዛቸውን ደብቀው ሰላማዊውን ህዝብ ሊነድፉ ተዘጋጅተዋል፡፡

አሁን እየታየ ያለው የተሟሟቀ የምርጫ እንቅስቃሴ አልዋጥላቸው ያሉ አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች #እኔ ከሞትኩኝ ሰርዶ አይብቀል; አይነት አባባልን በመጠቀም ሕዝቡን ውዥንብር ውስጥ ለመክተት ይጣጣራሉ፡፡ በ1997 ዓ.ም. በተደረገው ሦስተኛው አገራዊ ምርጫ ላይ የተስተዋለውን አይነት ስህተት ዛሬም ለመድገም ወገባቸውን አጥብቀው የተነሱ ይመስላል፡፡ ሁሉንም ነገር ጥላሸት መቀባት የሚቀናው መድረክና ስብስቡ ስለምርጫው ምንም ዓይነት እንከን ባልታየበት ሁኔታ በጭፍን ‹‹ምርጫው ፍትሐዊ አይሆንም ›› ፣ ‹‹በመጪው ምርጫ እኔ ካላሸነፍኩኝ የምርጫው ኮሮጆ ተሰርቋል ማለት ነው ›› በማለት ተቀባይነት የሌለው መላምት መንዛት ምርጫው ሰላማዊ እንዳይሆን ከማደናቀፍ የዘለለ መልካም ውጤት ይኖረዋል ተብሎ ሊታመን አይችልም፡፡ በህዝባዊ አስተሳሰብ አይን ሲታይ ገና የምርጫው ፉክክርና የምረጡኝ ቅስቀሳው ሳይጀመር

ማንም ቢሆን ስለማሸነፉና መሸነፉ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይችልም፡፡ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት የዘነጋ ካልሆነ በስተቀር፡፡

በጣም የሚገርመው ደግሞ በኢህአዴግ ጥላ ሥር ሲታገል የነበረና በአመራርነት ሲሰራ ከነበረ ፖለቲከኛ አቶ ስዬ አብርሃ ይህን መሰል ነገር መስማቴ ብዙ ነገር እንዳስብ አድርጎኛል፡፡ በአመራርነት ሲሰሩ በነበረበት ወቅት ሥርዓቱን ባለመቀበል አፈንግጦ መውጣት ለምን አልቻሉም ነበር? ባጠፉት ጥፋት ወደ ማረሚያ ቤት ወርደው ስለነበር ለዚያ ብቀላ በሚያስመስል መልኩ ያዩትን መልካም ነገር ሁሉ ማጥላላትና ማጣጣል ተያይዘውታል፡፡ ይህን ጥያቄ ላነሳ የቻልኩት ያለምክንያት አይደለም፤ ህወሐት የጣለባቸውን አደራ አንክተው ከጣሉት በኋላ ዳግም ለሌላ እኩይ ተግባር መነሳት ምን ይሉት አባዜ ነው? ነገሩን ላስተዋለው በጣም ከባድ ነው፡፡ ምናልባት ይቅርታ አለመጠየቃቸው ዛሬም አንድ ዙር ጥፋት ላጥፋና በአንድ ላይ ንስሐ እገባለሁ ብለው ይሆን?

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ አመራር አባል የሆኑት አቶ ስዬ ‹‹ አራተኛው አገራዊ ምርጫ ከ35 ዓመት በፊት ከአፄው ሥርዓት ከነበረው ምርጫ ያነሰ ነው ›› የሚል መግለጫ መስጠታቸው ዘመኑ የደረሰበትን ደረጃ በግልጽ አለመረዳትን ከማመልከቱም በላይ በእኔ እምነት የፊውዳል ሥርዓት ናፋቂ ከመሆን የዘለለ ትርጉም አይኖረውም፡፡ የሕዝብ ተሳትፎ በምንም መልኩ ያልነበረበት፣ የንጉሣውያን ቤተሰቦች እርስ በእርስ የሚመራረጡበትን የምርጫ ሥርዓት፤ ህዝቡ የመምረጥና የመመረጥ መብቱን ተጠቅሞ ይበጀኛል፣ ያስተዳድረኛል የሚለውን አካል በድምፁ ከሚያረጋግጥበት ዘመን ጋር ማወዳደር ምን የሚሉት አካሔድ እንደሆነ ሊገባኝ አልቻለም፡፡ ምርጫው ተቀዛቅዟል ብለው ልባቸውን ሞልተው ሲናገሩ በምን መንገድ መዝነውት ይሆን? የግድ የምርጫው ሂደት ተሟሙቋል ለማለት ፓርቲዎች እና ግለሰቦች በየአደባባዩ መዘላለፍ ነበረባቸውን? ሁከትና ብጥብጥ መንገስ አለበትን? ምናልባት የሥልጣን ጥምን ለማርካት የሚንቀሳቀስ ኃይል ወቅቱ አልፈቅድለት ስላላቸው እንጂ ብጥብጥና ሁከትን በመጠቀም ሥልጣን ኮርቻ ላይ ለመፈናጠጥ አማራጭ መንገድ መፈለግ ይመስለኛል፡፡

ቁምነገር ሠርቶ ከህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን ማግኘት ሲገባ ጆሮ ኮርኳሪ ንግግሮችን በመሰንዘር የሌሎችን ስምና ዝና ለማጉደፍ የዘወትር ሥራ አድርጎ መነሳት የዋህነት ነው፡፡ ‹‹መልክ ስጠኝ እንጂ ሙያንስ ከጐረቤት እማራለሁ›› ሲባል ተሰማና ‹‹ሥልጣን

ስጠኝ እንጂ ለህዝብና ለሀገር ቀስ ብለን እናስብበታለን›› የሚል ተማፅዕኖ ማሰማት ይመስላል እየታየ ያለው አካሔድ፡፡ የአንዳንድ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ራዕይና ግብ በምንም መንገድ ወደ ሥልጣን የሚያበቃቸውን መንገድ መቀየስ ነው፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ አገራችን የጀመረችውን የልማትና የዴሞክራሲ ሂደት የሚቃረን ነው፡፡

በ97ቱ ምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ሲነገሩ እንደነበሩት ንግግሮች ዛሬም ‹‹እኔ ካላሸነፍኩኝ ምርጫው ተጭበርብሯል; ማለት በሀገራችን ያሉትን ሌሎች ፓርቲዎችን ምንም እንደሌሉ መቁጠርን ያሳያል፡፡ ምንጊዜም ቢሆን ወደ ምርጫ ሲገባ አሸናፊና ተሸናፊ እንዳለ መታወቅ አለበት፡፡ አሸናፊውን የሚወስነው ደግሞ ህዝቡ በሚስጥር በሚሰጠው ድምጽ ነው፡፡ እኔ ካላሸነፍኩ በማለት የምርጫውን ሂደት ጥላሸት መቀባት አንድም የሕዝብን ሉዓላዊነት መድፈር ያስመስልባቸዋል፡፡

ስለዚህ ለህዝብና ለሀገር የሚጠቅመው ፓርቲዎች ከመላምትና ፍሬ ከሌለው ግምት ርቀው የምርጫ ፉክክሩን ሰላማዊና ፍትሐዊ እንዲሆን ጠንክረው ሲሰሩ ነው፡፡ የምርጫ ዴሞክራሲያዊነት የሚለካው በውጤቱ ብቻ ሳይሆን በሒደቱ መሆኑን ተገንዝበው መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ጊዜው መንገድ የጠፋበትን መከተልን ሳይሆን ፀሐይ የወጣለትን መከተልን ያስተምራል፡፡